# Car seats, booster seats, and seat belts keep children safe in the car

Age of child (years)






**Rear-Facing Car Seat** must be used for babies and toddlers. Use a carrier-type or a convertible seat until baby's head is one inch below back of seat. Don't turn convertible seat forward until baby meets weight & height limits listed for rear-facing car seat use.



**Forward-Facing Car Seat** with a harness is used when the rear-facing seat limits for age, height or weight are reached. Use this seat until child is 6 or 7 years old or reaches the seat's limits. Also, use the tether strap on car seat to secure top of seat to car.



**Booster:** Use a booster with the car's seat belt once your child has outgrown the harnessed seat. Use this until age 8 or until your child fits the seat belt properly. For most kids, this is about age 10 and 4 foot 9 inches tall.



**Seat Belt:** Use the car's lap and shoulder parts of the seat belt for every ride. Proper fit is sitting all the way back with knees bent at edge of cushion, lap belt across upper thighs not on the stomach, and shoulder belt across chest and collarbone.

Maryland requires children under 8 years old to ride in a car seat unless the child is 4 feet, 9 inches or taller. Every child from 8 to 16 years old not in a car seat must use a seat belt.

**Always read the car seat manual to learn how to adjust the seat and secure it in your car.**

## For help with getting or using a car seat with your child and your car:

### Maryland Kids in Safety Seats

**MD Department of Health**

**Call: 443-842-0508**

**Email: mdh.kiss@Maryland.gov**

**Contact online: www.mdkiss.org**

### Online videos to teach use of car seats:

**https://www.nhtsa.gov/equipment/car-seats-and-booster-seats**

## የመኪና ውስጥ ተጨማሪ መቀመጫዎ፣ የልጆች ደጋፊ መቀመጫዎች እና የመኪና ቀበቶዎች በመኪና ውስጥ የልጆችን ደህንነት ይጠብቃሉ

### የልጁ ዕድሜ (ዓመት)






**ወደ ጀርባ የሚዞር የመኪና ውስጥ መቀመጫ** ለጨቅላ ሕፃናት እና ዕድሜያቸው እስከ ሶስት ለሚደርስ ሕፃናት መጠቀም ያስፈልጋል። ከመቀመጫው የሕፃኑ ጀርባ አንድ ኢንች ያነስ እስኪሆን ድረስ የማዳዳዣ ዓይነት ወይም ኮንቨርተብል መቀመጫዎችን ይጠቀሙ። ወደ ጀርባ የሚዞር የመኪና ውስጥ ማስቀመጫ የተቀመጡት የክብደት እና የቁመት ወሰኖች ላይ ሕፃኑ/ኗ እስከሚደርሱ ድረስ ኮንቨርተብል መቀመጫዎችን ማዞር የለብዎትም።



**ወደ ፊት የሚዞር የመኪና ውስጥ ማስቀመጫ**

ከመጠፈሪያ ጋር የሚያገለግለው ለዕድሜ፣ ቁመት ወይም ክብደት ወደ ጀርባ ማዞር የመኪና ውስጥ ማስቀመጫ ወሰኖች ላይ ሲደረስ ነው። ይሄንን ማስቀመጫ ልጁ/ልጅቷ 6 ወይም 7 ዕድሜ እስኪሞላቸው ወይም የመቀመጫው ወሰን ላይ እስከሚደርሱ ይጠቀሙት። እንዲሁም፣ የመቀመጫውን ጫፍ ከመኪናው ጋር ለመጠፍር ቴዘር ገመድ ከማስቀመጫው ጋር ይጠቀሙ።



**ደጋፊ መቀመጫዎች:-**

ልጅዎ የተጠፈረውን መቀመጫ በላይ ያደገ ከሆነ ከመኪናዎት ቀበቶ ጋር ደጋፊ ማስቀመጫ ይጠቀሙ። ይሄንን እስከ 8 ዓመት ዕድሜ ድረስ ይጠቀሙ ወይም የመኪና ቀበቶው ላይ በሚገባ ጠብቆ እስከሚቀመጥ ድረስ። ለአብዛኛዎቹ ልጆች፣ ይሄ ዕድሚያቸው 10 እስከሚሞላ እና ቁመታቸው 4 ጫማ እና 9 ኢንች እስከሚደርስ ነው።



**የመኪና ቀበቶ:-**

ሁልጊዜ መኪና ሲነዱ የመኪናውን የታፋ እና የትከሻ የመኪና ቀበቶ ክፍሎችን ይጠቀሙ። በሚገባ አጥብቆ መቀመጥ ማለት የሰፋው ጫፍ ላይ ጉልበቶች እንደታጠፉ፣ የታፋ ቀበቶ በሆድ ላይ ሳይሆን በላይኛው የታፋ ክፍል ላይ ሲሆኑ፣ እና የትከሻ ቀበቶ ደግሞ ደረትን እና የጎን አጥንትን አቋርጦ ሲታሰር ነው።

የሜሪላንድ ሕግ ልጅ/ቷ 4 ጫማ እና 9 ኢንች ወይም ከዚያ በላይ እስካልሆኑ ድረስ ዕድሚያቸው ከ 8 ዓመት ያነሱ ልጆች የመኪና ውስጥ ማስቀመጫ እንዲጠቀሙ ያስገድዳል። በመኪና ውስጥ ማስቀመጫ ላይ ያልተቀመጠ ዕድሚያቸው ከ 8 እስከ 16 የሚደርስ ልጆች የመኪና ቀበቶ ማጥለቅ አለባቸው።

**የመኪና ውስጥ መቀመጫውን እንዴት እንደሚያስተካክሉት እና መኪናዎት ላይ እንዴት እንደሚያጠብቁት ለማወቅ መመሪያ ያንብቡ።**

### ከልጅዎ እና ከመኪናዎ ጋር የመኪና ማስቀመጫዎችን ማግኘት ወይም አጠቃቀም ላይ እገዛ ከፈለጉ:-

**የሜሪላንድ ልጆች አስተማማኝ መቀመጫ ላይ**

**MD የጤና መምሪያ**

**ይደውሉ:- 443-842-0508**

**ኢሜይል:- mdh.kiss@Maryland.gov**

**ኦንላይን እዚህ ይጎብኙ: www.mdkiss.org**

**የመኪና ውስጥ ማስቀመጫዎችን አጠቃቀም ላይ የማስተማሪያ ኦንላይን ቪዲዮዎች:-**

**https://www.nhtsa.gov/equipment/car-seats-and-booster-seats**

Amharic